EFDA
የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

ከኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ጥበቃ እና ጠበቃ ለፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች

የፀረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በቫይረስ፣ በባክቴሪያ፣ በፈንገስና በፕሮቶዝዋ አማካኝነት የሚመጡ በሽታዎችን ለማከምና ለመከላከል የሚያገለግሉ ናቸው:: የፀረ ተህዋስያን መድኃኒቶች ግኝት የሰው ልጅ ካስመዘገባቸው የታሪክ እምርታዎች አንዱ ሲሆን እነሱም በሽታ አምጪ ተህዋስያንን በመግደል ወይም እድገታቸውን በመግታት የሰውንና የእንስሳትን ኢንፌክሽን (ተላላፊ በሽታዎች) ለመከላከልና ለማከም የምንጠቀምባቸው ወሳኝ መድኃኒቶች ናቸው::

### የፀረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መስመድ እንዴት ይከሰታል?

የፀረ ተህዋስያን መድኃኒቶች ጀርሞቹን ለማስወገድ ትክክለኛው መድኃኒት በበቂ መጠንና ጊዜ መገኘት ሲኖርበት ይህ ካልሆነ ለመላመድ እድል ስለሚሰጣቸው መድኃኒቶቹን እንዲመክኑ/ውጤታማ እንዳይሆኑ ይዳርጋል። በሽታ አምጭ ጀርሞች የፀረ ተህዋሲያን መድኃኒቶችን መልመድ ጀርሞቹ ለመኖር ሲሉ ራሳቸውን ለመከላከል የሚፈጥሩት የተፈጥሮ ሂደት ነው/ ዝርዝር አካሄዱ ሰፋ ያለ ሳይንሳዊ ትንታኔ ስላለው ከዚህ ጸሁፍ ወሰን በላይ በመሆኑ ታልፏል:: የጸረ ተህዋስያን መድኃኒቶች እንክብካቤና ጥበቃ እንዲሁም አላግባብ አጠቃቀማቸውን የሚገድብ ሕግና ጠበቃ ያስፈልጋቸዋል እንላለን።

### የፀረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መስመድን የሚያባብሱ ጉዳዮች ምንድናቸው?

ጸረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በስፋት እና አለአግባብ ጥቅም ላይ ሲውሉ መላመዱን ያፋጥናሉ፣ መድሃኒት በሚያዝዙ ወይም የታዘዘን መድኃኒት በሚያድሉ/የመድኃኒት ባለሙያዎች ወይም በራሱ በተጠቃሚው አማካይነት ሊሆን ይችላል። ይህንን ከሚያባብሱ ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- ስለ ችግሩ ምንነት፣ ምክንያት ግዝፈትና የመፍትሔ ርምጃዎች ላይ የግንዛቤ እጥረት
- ፀረ-ተሕዋስያንን አላግባብ መጠቀም፤ ማለትም ከመጠን ማሳነስ፣ ማስበለጥ ወይም የታዘዘበትን የመድኃኒት መውሰጃ ሰዓትን ማዛባት፤
- ህመሙ የተሻለን ሲመስለን የታዘዘን የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒት ማቋረጥ
- ለሰውም ሆነ ለእንስሳት የንፁህ ውሃ፣ የግል እና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅ ጉድለት ይተቀሳል::

### ስለ የጸረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መስመድ መዘዙ

የፀረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ኢንፌክሽኖችን ለማከም የምንጠቀምባቸውን የመድኃኒት አማራጮችን እና እድሎችን ያጠባል:: ምክንያቱም ቀድሞ በፈዋሽነቱ ውጤታማ የነበረን መድኃኒት አሁን ግን በበሽታ አምጪው ተህዋስ መላመድ ምክንያት አገልግሎት ላይ የማይውልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ጥቅም መስጠት አይችልም:: በዓለም አቀፍ ደረጃ በዓመት ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ሰዎች በላይ በፀረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ምክንያት የሚሞቱ ሲሆን ወደ አምስት ሚሊዮን ሰዎች ደግሞ ከዚህ ጋር ተያያዥ በሆነ ምክንያት ይሞታሉ፣ ከዚህም 41 ነጥብ አምስት በመቶ ድርሻው በአፍሪካ እንደሆነ ተመላክቷል:: በኢኮኖሚም እስከ ሶስት ነጥብ አምስት በመቶ ዓመታዊ ምርት ቅነሳን ያስከትላል::

በዓለማችን ኢትዮጵያም ጭምር አሁን አሁን በተግባር እየታዩና ውስብስብ ችግር እየሆኑ የመጡ ሌሎች ተጨባጭ ምሳሌዎችን መጥቀስ አስፈላጊ ነው:: ይኸውም የወባና የቲቢ በሽታ አምጭ ተህዋሳት ከፀረ ተህዋሳቱ መድኃኒቶች ጋር እየተላመዱ የመምጣታቸው አሳሳቢ ጉዳይ ነው::

በመሆኑም ከመዘዞቹ ውስጥ በበርካታ ሰነዶች ከተዘረዘሩት አንዳንዶቹን ለመምዘዝም

- የጸረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ዛሬ ለዓለም ጤና፣ የምግብ ዋስትና እና ልማት ትልቅ ስጋት/ለዘላቂ የልማት ግቦች እንዳይሳኩ እንቅፋት/መሰናክል መሆን፤
- የጸረ ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድ ማንኛውንም ሰው፣ ማንኛውንም ዕድሜ፣ ማንኛውንም አገር ሊያጠቃ ይችላል፤
- ተላላፊ በሽታዎችን በቀላሉ እና በመለስተኛ ወጪ ማከምና ማዳን አስቸጋሪ ይሆናል:: ከፀረ ተህዋሲያን መድኃኒቶች ጋር የተላመዱ በሽታ አምጭ ጀርሞች በህብረተሰቡ ውስጥ ከአንዱ ወደ ሌላው ስለሚተላለፉ የህብረተሰብ ችግር ይሆናል::
- በመጨረሻም ማዳን አልቻል ሲል ለሞት ይዳርጋል::

### ታዲያ ምን እናድርግ?

ስለ ፀረ ተህዋስያን መድኃኒት መላመድ ምክንያትና መዘዝ በአጭሩ ይህን ያህል ካልን መከላከል የምንችልባቸውን ሁኔታዎችን መነጋገሩም አስፈላጊ ነው:: ይህንንም በተለያየ ክፍለን ለማሳየት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### ህብረተሰብ

የፀረ- ተህዋስያን መድኃኒት መላመድ ዋናው መንስዔ በአጠቃቀም ችግር በመሆኑና ህብረተሰብ በአብዛኛው የመድኃኒቶች ተጠቃሚ በመሆኑ በግዢ፣ አያያዝና አጠቃቀም ላይ በርካታ ድርሻዎች ይጠበቃል፣ ለመጥቀስም -

- የጸረ ተህዋስያን መድኃኒቶችን ያለ ሐኪም ተዕዛዝ አለመጥቀም፣ በጸረ ተህዋስያን መድኃኒቶች ራስን በራሱ አለማከም
- የታዘዘልንን መድኃኒት በተለይ አሳንሶ መውሰድ (በአንድ ጊዜ የሚወሰደውን መጠን ቀንሶ አለመውሰድ ወይም ሳይጨርሱ አለማቋረጥ)

### የሰውና የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች

የጤና ባለሙያዎችም የታካሚውን በሽታ ምንነት በሚገባ ተገንዝበው ትክክለኛውን መድኃኒት መርጦ በማዘዝና ስለመድኃኒቱ ትክክለኛና አስፈላጊውን መረጃ ለተገልጋዩ በመግለጽ ማደል አለባቸው::

- በጤና ተቋማት ኢንፌክሽንን መከላከል
- ፀረተህዋሲያን መድኃኒቶችን አስፈላጊ ሲሆን ብቻ በሥርዓቱ በተቀመጠው መሠረት ማዘዝና ማደል፣

### ፖሊሲ አውጪዎችና ተቆጣጣሪ አካላት/የጸረ ተህዋስያን መድኃኒቶች ጠባቂ

የመድኃኒት ጥራት ቁጥጥር አካላትም የፀረ ተህዋስያን መድኃኒት መላመድን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ላይ ከፍተኛ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል:: በተለይ በጥቁር ገበያ / black market/ የሚገኙና ጥራት የጎደላቸውን መድኃኒቶች የሚያቀርቡ ድርጅቶችን በመከታተል ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ መውሰድ ይገባል::

- የፖሊሲና የሕግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፣ መከለስ፣ አፈጻጸማቸውን መከታተል
- በየሴክተሩ ችግሩን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ እቅዶች እንዲካተቱ ማድረግ

### መገናኛ ብዙኃን

መገናኛ ብዙኃን የህዝብ አይን፣ ጆሮና አንደበት እንደመሆናቸው መጠን ችግሩን መቃኘት፣ ማጤን፣ ማንቃትና ማስገንዘብ የሚጠበቅ ሲሆን በተለይም፤

- ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በጉዳዩ እንዲንቀሳቀሱ የማንቂያ ደወሉን በየጊዜውና በተደጋጋሚ ማስተጋባት፤
- በየተሰማሩበት የሚዲያ ዘርፍ (ህትመት ወይም ኤሌክትሮኒክስ፤ በመንግሥትም ሆነ በግል) ለህብረተሰቡ ስለ ጸረ-ተህዋስያን ብግርነት፣ አግባባዊ የመድኃኒት አጠቃቀም፣ ኢንፌክሽንን ስለመከላከልና ተያያዥ ጉዳዮች በተደጋጋሚ ማሳወቅ/ ማስተማር

የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶች በጀርሞች መለመድን መከላከልና መቆጣጠር አጣዳፊ አደጋ በመሆኑና ማንንም ሊያጠቃ የሚችል ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ የጤና፣ የኢኮኖሚና የሴኩሪቲ ስጋት ነው። ዛሬ የመከላከል እና የመቆጣጠር እርምጃው ላይ ካልተረባረብን የነገው ህልውናችን አደጋ ላይ ነው:: ሥራውም ለአንድ አካል ብቻ የምንተወው ሳይሆን ከሁሉም ርብርብን የሚጠይቅ በመሆኑ ሁላችንም የፀረ-ተህዋስያን መድኃኒቶችን የመጠበቅ እና ጠበቃ የመሆን ድርሻችንን ልንወጣ ይገባል እንላለን::

Tel : +251-11-552-41-22
+251-11-552-41-22
P.o.box. 5681
Free call. 8482

http://www.fmhaca.gov.et/contact/
E-mail contactefda@efda.gov.et
Telegram channel link
https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/